# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከፌብሪዋሪ 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከፌብሪዋሪ 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌበርዋሪ 2022
አዲስ አበባ

ማስታወሻ

እባክዎ http://www.ethiomet.gov.et ይጎብኙ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ........ 4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 4

እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ........ 5

በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 5

እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ . 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 6

እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 11 እስከ 20/2022 የሚኖረው የአየር ........ 7

ሁኔታ አዝማሚያ ........ 7

እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 11 እስከ 20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 7

እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 11 እስከ 20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8


## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቅና ፀሃያማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በመጀመሪያዎቹ የተወሰኑ ቀናት በሰሜን፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብና ምስራቅ ደጋማ ስፍራዎች ላይ አይሎ የተስተዋለ ሲሆን፤ የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀትም በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከ5 ዲ.ሴ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በደብረብርሃን -1.0፣ በሐረማያ 1.0፣ በአምባ ማሪያም 3.0፣ በመሃል ሜዳ 3.5 እና በቡኢ 4.4 በዲ.ሴ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል ከአስሩ ቀናት አጋማሽ በኋላ አንጻራዊ የሆነ የደመና ሽፋን መጨመር በመስተዋሉ ቅዝቃዜዉም ጋብ ያለበትና በምስረቅ አማራ፣ በምዕራብ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ጥቂት ቦታዎች ላይ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገባቸዉ እንደ ነበር በግምገማዉ ለመረዳት ተችሏል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በሰሜንና ደቡብ ጎንደር ፣ በጅማ፣ በቤንች ማጂ፣ በሸካና ከፋ ዞኖች ጥቂት ቦታዎች ላይ እስከ 50 ሚሜ የሚደርስ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ዘንቧል (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በሰሜንና ደቡብ ጎንደር እንዲሁም ሸካ ዞኖች በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ ከተመዘገበዉ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ በስተቀር የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በደረቅ የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# ኢ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የፌብሪዋሪ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ አመዝኖ የሰነበተ ነበር፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በመጀመሪያዎቹ የተወሰኑ ቀናት በሰሜን፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብና ምስራቅ ደጋማ ስፍራዎች ላይ አይሎ የተስተዋለ ቢሆንም በመስኖ በሚለሙ የደጋ ሰብሎች፣ በቋሚ ተክሎችም ሆነ በጓሮ አትክልቶች ላይ ያን ያህል አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳልነበረው ነው። ነገር ግን ከአስሩ ቀናት አጋማሽ በኋላ አንጻራዊ የሆነ የደመና ሽፋን መጨመር በመስተዋሉ ቅዝቃዜዉም ጋብ ያለበትና በምስረቅ አማራ፣ በምዕራብ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ጥቂት ቦታዎች ላይ መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው። ይህም የተገኘው እርጥበት በተለይም የበልግ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማድርግ በተወሰነ መልኩ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነበር (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 ኢ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-10 ፌብሪዋሪ 2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ ስንመለከት በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ተስተዉሏል፡፡ ነገር ግን በጥቂት መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ ፣አፋር ደናክል እና በጥቂት መካከለኛው ተከዜ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸው (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5  እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 11 እስከ 20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የፌብሪዋሪ ሁለተኛ አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት እና የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የሚጠናከሩበት ጊዜ ነው፡፡ ስለሆነም የደቡብ ምዕራብ" የመካከለኛው" የሰሜን ምሥራቅና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ዝናብ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት አሁን እየተስተዋለ ያለዉ ደረቃማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከሞላ ጎደል ቀጣይነት እንደሚኖረዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት መጠነኛ የደመና ሽፋን በስምጥ ሸለቆና አጎራባች በሆኑት አካባቢዎች ላይ ሊኖር እንደሚችል ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት <u>ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ ጅማና ኢሉባቦር፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በሸካ፣ ከፋና ቤንች ማጂ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ ሰሜን ሸዋ ዞን ጨምሮ፣ ከትግራይ ክልል ደቡብ ትግራይ፣ ከአፋር ክልል ዞን 02ና 04፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በስልጤ፣ ጉራጌና ሐዲያ ዞኖች ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖራቸዉ እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ፡፡</u>

## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 11 እስከ 20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የፌብርዋሪ ሁለተኛዉ አስር ቀናት የበልግ ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ላይ ዝናብ የሚጀምርበት ከዚህም ጋር ተያይዞ የማሳ ዝግጅት እንቅስቃሴዎች የሚጀመሩበትና አስቀድመው ለሚዘሩ አካባቢዎችም የዘር ወቅታቸው ነው።

ከላይ በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት የፌብርዋሪ ሁለተኛው አስር ቀናት አሁን እየተስተዋለ ያለዉ ደረቃማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከሞላ ጎደል ቀጣይነት እንደሚኖረዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በስምጥ ሸለቆና አጎራባች በሆኑት አካባቢዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህም የሚገኘው መጠነኛ እርጠበት በተለይም የበልግ አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የማሳ ዝግጅት ለማድርግ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። በመሆኑም የበልግ ሰብል አብቃይ የሆኑ አርሶ አደሮች ሊገኝ የሚችለውን አነስተኛ እርጥበት በመጠቀመ አስፈላጊውን ዝገጅት አስቀድመው በማድረግ የማሳ ዝግጅት ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ከወዲሁ እንዲያደርጉ ይመከራሉ።

## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 11 እስከ 20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ፌብርዋሪ ሁለተኛው አስር ቀናት  የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ የደቡብ ምዕራብ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን ምሥራቅና የምሥራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የላይኛው ተከዜ፣ የላይኛው እና መካከለኛው አባይ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ ኦሞ ጊቤ እና ስምጥ ሸለቆ አዋሳኝ እና የላይኛው እና ታችኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖራቸዉ ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ የሚያመዝን በመሆኑ አልፎ አልፎ የሚገኘውን አነስተኛ እርጥበት ጥቅም ላይ ለማዋል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን እንጠቁማለን፡፡